ቁጥር OFAGF 03.24/4/4
ቀን 6/07/2015

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA
OFFICE OF THE FEDERAL
AUDITOR GENERAL

ለክብርት ወ/ሮ አለምፀሐይ ጳውሎስ

የጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ኃላፊና የካቢኔ ጉዳዮች ሚኒስትር

ለክቡር ዶ/ር ሣሙኤል ኡርቃቶ

የፌዴራል ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር

<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ:- <u>የፌዴራል ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት ይመለከታል፤</u>

የፌዴራል ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ውጤትና አስተያየት የያዘ 14 ገጽ የኦዲት ሪፖርት እና 14 ገጽ የሂሣብ ሪፖርቶች በድምሩ 28 ገጽ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

አበራ ታደሰ
የፌዴራል ም/ዋና ኦዲተር

Office of the Federal Auditor General

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የፌዴራል ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን

የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ
ኦዲት ሪፖርት

መጋቢት/2015

አዲስ አበባ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የፌዴራል ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን

የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ

ኦዲት ሪፖርት

የፌዴራል ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን የተመደበለትን የመደበኛ እና የካፒታል በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሰረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የፌዴራል ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ስራ አመራር ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው ::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ስልጣን ሲሆን ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች በመከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፡-

- በሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና ሪፖርቶችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶች ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል::

ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦች እና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑንና በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይይዛል፡፡
ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት የፌዴራል ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በመ/ቤቱ ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው::

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡
የሚከተሉት የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

- የገቢ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የሂሳብ ማመዛዘኛ፣

ለኦዲት አስተያየቱ መሰረት የሆኑት ጉዳዮች፣

የፌዴራል ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን የ2014 በጀት ዓመት የሂሣብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት በመንግሥት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በትክክል የተዘጋጁና፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. ከመመሪያ ዉጪ ለሹፌሮች የተከፈለ የተሽከርካሪ ማሳደሪያ እና ማጽጃ ክፍያን በተመለከተ፤

የፌዴራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 ክፍል ሁለት የመንግስት መ/ቤት አደረጃጀት፣ የስራ ምዘና፣ የደሞዝ ስኬል እና አበል አንቀጽ 10 ንኡስ አንቀጽ 2 ሚኒስቴሩ የአበል ዓይነቶች እና ክፍያዎችን እያጠና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ለውሳኔ ያቀርባል፤ ሲፈቀድም አፈጻጸማቸውን ይቆጣጠራል በማለት ይደነግጋል፡፡

ይሁን እንጂ በተሻሻለው የፌዴራል የስነ-ምግባር የጸረ-ሙስና ኮሚሽን የትራንስፖርት አገልግሎት እና ነዳጅ አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 14/2013 አንቀጽ 18 ንኡስ አንቀጽ 4 እና 5 ሹፌሮች ተሽከርካሪዎችን ለማሳደር ከግል ኪሳቸው ማውጣት የሚጠበቅባቸው ስላልሆነ የመኪና ደህንነት አሽከርካሪዎች በግል ኃላፊነት የሚወስዱ ሆኖ ለጥበቃ በወር 500 እንዲሁም ለኮሚሽኑ የበላይ ኃላፊዎች ለተመደቡ ሹፌሮች በየዕለቱ የተሽከርካሪውን ንጽህና ለመጠበቅ እንዲያስችል በየወሩ ብር 500 እንዲከፈላቸው በውስጥ ቁጥጥር ስርዓት በኮሚሽነሩ አማካኝነት በማጽደቅ ከደመወዛቸው ጋር እንዲከፈል በማድረግ በድምሩ ብር 162,500.00 ከመመሪያ ውጭ ያለአግባብ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

2. መንግስትን ለተጨማሪ ወጪ የዳረገ ግዥን በተመለከተ፤

የፌደራል መንግስት ግዥ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ 2002 በወጣው ክፍል አንድ አንቀጽ 4 ፊደል ሀ በግዥ አፈጻጸም ረገድ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም ማስገኘት እንደሚገባ ይህም ማለት ቁጠባን ፣የአፈጻጸም ብቃትን እና ውጤታማነትን ማረጋገጥ እንዳለበት መመሪያው ይገልፃል፡፡ ይሁን እንጂ ፡-

በቀን 11/04/2013 ጨረታ ቁጥር 010/2013 ለኮሚሽኑ ተሽከርካሪዎች አገልግሎት የሚውሉ የተሽከርካሪ ጎማና ባትሪ ግዥ ለመፈጸም በወጣው ግልጽ ጨረታ የቴክኒክ ውድድሩን ያሸነፈውን ድርጅት ብቸኛ አቅራቢ በመሆኑ የገበያ የጥናት ዋጋ በተጠናው መሰረት አቅራቢ ድርጅት ካህሳይ ጎማና ባትሪ መሸጫ ያቀረበው ዋጋ ከገበያ ዋጋ ጋር ሲነጻጸር ብልጫ ባሳዩት የተወሰኑ ጎማዎች ላይ ጨረታው ውድቅ ሆኖ በሌሎች የግዥ ዓይነቶች ግዥው እንዲፈጸም በቀን 13/05/2013 የግዥ ቡድን በሰጠው ሃሳብ መሰረት በግዥ አጽዳቂው ኮሚቴ የጸደቀና የገበያ ጥናት ዋጋ ተጋኗል ተብሎ የተወሰነ ቢሆንም ግዥው በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ ሲፈጸም ከጨረታ ዋጋ እና ወቅታዊ ከገበያ ጥናት ዋጋ በላይ ግዥውን በማከናወን በብልጫ በድምር ብር 299,961.25 ያለአግባብ መንግስትን ለተጨማሪ ወጪ የዳረገ መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

3. <u>ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበው ሳለ ከፍተኛ ያቀረበው አቅራቢ አሸናፊ ተደርጎ የተመረጠ ግዥን በተመለከተ</u>

የፌደራል መንግስት ግዥ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ 2002 በወጣው ክፍል አንድ አንቀጽ 16.19.2.1 የመንግስት መ/ቤቱ አሸናፊውን ተጫራች ለመምረጥ የመጀመሪያ ደረጃ ግምገማ የተቀበለባቸውን የመጫረቻ ሰነዶች እና የጨረታ ሰነዱ ላይ የተገለጹትን መስፈርቶች ተጠቅሞ ዝርዝር ግምገማ ማድረግ አለበት፡፡ በጨረታ ሰነዱ ውስጥ ከተገለጸው መስፈርት ውጭ ግምገማ ማድረግ አይፈቀድም በማለት ይገልጻል፡፡

ይሁን እንጂ ኮሚሽኑ በግዥ መለያ ቁጥር 011/2013 በቀን 11/04/2013 ዓ.ም በሪፖርተር ጋዜጣ በወጣው ግልጽ ጨረታ ላይ የግዥ ቡድን አባላት በቀን 18/05/2013 ጨረታውን በገመገሙበት ቃለ ጉባኤ ላይ ጨረታው ከተሳተፉ አቅራቢዎች መካከል ደስታ መሰረትና ጓደኞቹ የአልሙኒየም ማምረቻ በጨረታ ሰነዱ ምዕራፍ 1 ክፍል 3 እና ክፍል 6 መሰረት ድርጅቱ አሟልቶ የላከ ቢሆንም ድርጅቱ ስራውን ሰርቶ ለማስረከብ ያለውን አቅም ቦታው ድረስ በመሄድ ለማየት ቢሞከርም በአድራሻው የተጠቀሰው የራሱ ሳይሆን የሌላ ድርጅት በመሆኑ ውድቅ ተደርጓል በማለት ተገልጿል፡፡ በመሆኑም ደስታ፣መሰረትና ጓደኞቹ የአልሙኒየም ማምረቻ የጨረታ ሰነዱ በመክፈቻ ስነ-ስርዓቱ ወቅት በመጨረቻ ሰነዱ ላይ የተዘረዘሩትን ቅድመ ሁኔታዎችና

አስፈላጊ ነጥቦች ያሟላ እና የፋይናንሽያል ግምገማ በማለፍ ዝቅተኛ ዋጋ ብር 998,298.60 አቅርቦ ማሸነፍ ሲኖርበት በጨረታ ሰነዱ ውስጥ ከተቀመጠው መገምገሚያ መስፈርት ውጭ ከጨረታው ያለአግባብ እንዲወጣ የተደረገ በመሆኑ፣ ጨረታውን ሰላም የህጻናት መንደር ኢንዱስትሪያልና አግሪካልቸራል ኢንጅነሪንግ አሸናፊ አድርጎ በመምረጥ በቀን 21/06/2014 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 8826 በሂሳብ መደብ 2311102 ብር 1,292,659.99 ሰላም የህጻናት መንደር ኢንዱስትሪያልና አግሪካልቸራል ኢንጅነሪንግ ዕቃውን ገቢ እንዲያደርግ በመደረጉ ብር 294,361.39 መንግስትን ለተጨማሪ ወጪ የዳረገ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

4. በጀት ዓመቱን ያልጠበቀ ሂሳብን በተመለከተ፣

የፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የመደበኛና ካፒታል የስራ ማስኬጃ ወጪዎች ሲፈጸም ወጪው ለሚደረግበት ተግባር በበጀት ዓመቱ የተያዘ ወይም ወጪውን ለመሸፈን ቀሪ በጀት መኖሩንና ወጪው በመስሪያ ቤቱ ዕቅድ ውስጥ የተያዘና በጥሬ ገንዘብ ፍላጎት ላይ የተካተተ መሆኑ ሳይረጋገጥ ወጪ መፈፀም እንደማይገባ መመሪያው ይገልፃል፡፡ በዚህም መሠረት የሚፈፀሙ ክፍያዎች መመሪያውን የተከተሉ መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ፡-

በኮሚሽኑ ለድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ያልተከፈለ የስልክ ክፍያ እ.ኤ.አ ከነሃሴ 2014 እስከ 2015 በቀን 19/07/2014 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 8998 በሂሳብ መደብ 2241108 ብር 23,084.15 ክፍያ ሲፈጸም ክፍያው ረዘም ላሉ አመታት ሳይከፈል የቆየ በመሆኑና በወቅቱ ክፍያው ላለመፈጸሙ ምንም አይነት ማረጋገጫ ባልተገኘበት ሁኔታ እንዲሁም ከበጀት አመት ውጪ ክፍያ በመፈጸም ተመዝግቦ የተገኘ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

5. መነሻ የምዝገባ ሰነድ ማስረጃ የሌለው የተሰብሳቢ ሂሣብ

በፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 ፣ በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 የተሰብሳቢ ሂሳብ በአንቀጽ 8 ቁጥር 4 ከፊደል ሀ-ሰ በዝርዝር በተቀመጠው መሰረት በወቅቱ እየተሰበሰበ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

በኮሚሽኑ በ2014 በጀት ዓመት በሂሳብ ሪፖርት ላይ በተሰብሳቢ ሂሳብ የሚታየው:-

- ከመደበኛ ብር 5,322,352.11
- ከፕሮጀክት ብር 81,081.15

በድምሩ ብር 5,403,433.26 የሚታይ ሲሆን በእርጅና ዘመን ትንታኔ (aging analaysis) ያልቀረበ ከመሆኑም በተጨማሪ በተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት ላይ የሚታየው ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ መነሻ ሰነዱ ለኦዲት እንዲቀርብ በተደጋጋሚ ቢጠየቅም ሊቀርብ ባለመቻሉ በሪፖርቱ ላይ የሚታየውን የተሰብሳቢ ሂሳብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

6. <u>መነሻ የምዝገባ ሰነድ ማስረጃ የሌለው የተከፋይ ሂሳብ</u>

የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8/5 ፊደል ሀ መሠረት ማናቸውም ወደፊት ክፍያ የሚፈጸምባቸው ሂሳቦች ተከፋይ ሂሳብነታቸው የሚያረጋግጥ በቂ መረጃ ሲቀርብና ስልጣን ባለው አካል ሲፈቀድ በተከፋይ ሂሳብነት መያዝ እንደሚገባ ይገልጻል፡፡ በዚህ መሰረት የተከፋይ ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ:-

በኮሚሽኑ ሰኔ 30/2014 የተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት ላይ የመደበኛ በጀት ተከፋይ ሂሳብ ብር 8,477,935.32 የሚታይ ሲሆን በእርጅና ዘመን ትንታኔ (aging analaysis) ያልቀረበ ከመሆኑም በተጨማሪ በተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት ላይ የሚታየው ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ መነሻ ሰነዱ ለኦዲት እንዲቀርብ በተደጋጋሚ ቢጠየቅም ሊቀርብ ባለመቻሉ በሪፖርቱ ላይ የሚታየውን የተከፋይ ሂሳብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አለመቻሉ በኦዲት ታውቋል፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 6 በዝርዝር በተገለጹት ምክንያቶች በእኛ አስተያየት የፌዴራል ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሂሣብ ሪፖርቶች በበጀት ዓመቱ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ የተሰበሰበው ገቢ የተፈጸመው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳይም፡፡

ምንም እንኳ ከላይ የተሰጠውን የኦዲት አስተያየት የማይቀይረው ቢሆንም ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊሰጣቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች (Emphasise Matters)

1. **ሰኔ 30/2014 ሂሳብ ሪፖርት ላይ ባልተለመደ የሂሳብ ምዝገባ የሚታይ የፕሮጀክት ሂሳብ፣**

   የፌደራል መንግሥት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት የመንግሥት ሂሳብ አያያዝ አንቀጽ 8 ን/አ 8 ‹‹ሀ›› የሂሳብ ሪፖርት ከመዘጋጀቱ በፊት የአጠቃላይና የተቀጽላ ሌጀር ሚዛን ትክክለኛነቱ መረጋገጥ አለበት ‹‹ለ›› ትክክለኛነቱ የተረጋገጠው የአጠቃላይ ሂሳብ ሌጀር ሚዛን ወደ ገቢ፣ ወጪ፣ ዝውውር ተከፋይና ተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት ማድረጊያ ቅጽ ላይ በትክክል መተላለፍ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ በዚህ መሰረት የኮሚሽኑ የሂሳብ ሪፖርት በትክክለኛ የሂሳብ ሚዛን ሪፖርት መደረጉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በሰኔ 30/2014 ዓ.ም በሂሳብ ሪፖርት ላይ በሂሳብ መደብ 5212406 channel-2 Assistance Br. Account- clearing በGDPP ፕሮጀክት ብር 6,750.00 እና IPF ፕሮጀክት ብር 3,000.00 በድምሩ ብር 9,750.00 በዴቢት ሚዛን መታየት የነበረበት ባልተለመደ የሂሳብ ምዝገባ በክሬዲት ሚዛን የሚታይ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

2. **ሥራ ላይ ያለዋለ በጀት**

   የፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 ክፍል ሶስት አንቀጽ 12(1) ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ለበጀት ዓመቱ የተፈቀደለትን የመደበኛም ሆነ የካፒታል በጀት አጠቃቀም በሚገባ መቆጣጠር እንዳለበት ይገልጻል::በተጨማሪም በፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6/2 መሠረት የበጀት ዝውውር ወይም ተጨማሪ በጀት ካልተፈቀደ በስተቀር ለአንድ የመንግስት መ/ቤት በሂሳብ መደብ ተለይቶ ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ መፈፀም እንደማይቻል ይገልጻል፡፡ በዚሁ መሰረት የኮሚሽኑ በጀቱን የሚቆጣጠር መሆኑን ለማረጋገጥ የ2014 በጀት ዓመት ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተፈቀደው ከ10% በላይ ሥራ ላይ ከዋለው ጋር ሲነጻጸር፡-

በድምሩ ብር 505,158.18 ብር ከመደበኛ በጀት ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

3. <u>ያለሂሳብ መደቡ የተመዘገበ የወጪ ሂሳብ፤</u>

የፌዴራል መንግሥት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ዓ.ም በክፍል ሁለት አንቀጽ 6 ተራ ቁጥር 4 ላይ የመንግስት መ/ቤቶች በበጀት አደረጃጀት ሥርዓት መሠረት የተፈቀደላቸው በጀትና የወጣው ወጪ በሚያሳይ መልኩ ተለይተው በተሰጡዋቸው የበጀት መለያ መደቦች ተጠቅመው የሂሳብ እንቅስቃሴያቸውን መመዝገብ እንዳለባቸው ይገልጻል::በዚሁ መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ የወጪ ሂሳቦች ናሙና ተወስዶ ኦዲት ሲደረግ፡- ከመደበኛ በጀት ብር 3,529,593.42 እና ከፕሮጀክት ሂሳብ ብር 29,988.00 በድምሩ ብር 3,559,581.42 ያለ ሂሳብ መደቡ/አርዕስቱ በሌላ የሂሳብ መደብ /አርዕስት የተመዘገበ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

<u>ሌሎች ጉዳዮች (Other Matters)</u>

1. <u>የንብረት አመዘጋገብ ፣አያያዝ እና አጠባበቅን በተመለከተ፤</u>

የፌዴራል መንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 አንቀጽ 5 ግልጽ፣ ዘመናዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ የመንግስት ንብረት አስተዳደር በማስፈን፣ የመንግስት መ/ቤቶች በእጃቸው ያለውን የመንግስት ንብረት በጥንቃቄ መያዝ፣ የመጠቀም የመቆጣጠር እና አገልግሎቱ ሲበቃ ወይም አገልግሎት ላይ በማይውሉበት ጊዜ በወቅቱና በተገቢው መንገድ እንዲያስወግዱ ማስቻል እንዳለባቸው ይገለጻል፡፡ ይሁን እንጂ በአገልግሎት መ/ቤቱ ፡-

- የተለያዩ ተጠግነው አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ጠረጴዛ፣ ወንበሮች፣ መደርደሪያዎች፣ ከመዲኖዎች፣ የውሃ ማጣሪያ ማሽኖች፣ ሶፋዎች በደረጃ ላይ እና ኮሪደር ላይ ያለ ስራ የተቀመጡ መሆኑ፤
- የሚያገለግሉ ተለያዩ ዲስክ ቶፕ ኮምፒዩተሮች በተለያዩ ክፍሎች ውስጥ ያለስራ በብዛት ተከማችተው ያሉ መሆኑ፤
- ደስታ ወረቀት፣ የወረቀት መጠረዣ፣ ፋክስ ማሽን፣ በካርቶን የተቀመጡ አዳዲስ ንብረቶች፣ ዩፒኤስ(UPS) ብዛት ያላቸው ያለ አገልግሎት በተለያዩ ክፍሎች ውስጥ የተቀመጡ መሆኑ፤

- ንብረት ክፍሉ አንድ ንብረት ክፍል ሊይዝ የሚገባውን ምንም አይነት ማስረጃዎና መረጃዎች የሌለው እንዲሁም የንብረት አስተዳዳሪ ያልተረከበው መሆኑ፤
- አመታዊ የንብረት ቆጠራም ያልተደረገ መሆኑ፤
- ኮሚሽን መ/ቤቱ ሕንጻውን አሳድሶ ከገባ ጀምሮ ለንብረት ክፍል የሚያገለግለው የኢ.ፍ.ሚ.ስ(IFMIS) ስርዓት ያልተጀመረ መሆኑ፤
- የተወገዱት ንብረቶች በሰራተኞች እጅ የነበሩ በመሆናቸው ንብረቶቹን የተረከቡት ሰራተኞች ወደ ንብረት ክፍል ተመላሽ ሳያደርጉ ንብረቶቹ በስጦታ ለሌሎች ሴክተር መ/ቤቶች የተላለፉ መሆኑ፤
- በአጠቃላይ ከላይ የተጠቀሱት እንዳሉ ሆነው ለአላቂና ቋሚ ንብረቶች የተዘረጋ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓትና የተደራጀ ንብረት ክፍል አለመኖሩ፡ በኦዲት ታውቋል፡፡

2. <u>የተሽከርካሪዎች አስተዳደር በተመለከተ፤</u>

የፌዴራል መንግስት የተሽከርካሪዎች ስምሪት እና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2002 አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 የመንግስት መ/ቤት በግዥ፣በስጦታ በዝውውር ተረክቦ ለሚጠቀምበት ለዕያንዳንዱ ተሽከርካሪ የተለየ የግል ማህደር በመክፈት በማሕደሩ ውስጥ ቢያንስ የሚከተሉት መረጃዎች መዝግቦ ይይዛል፡፡ከ‹‹ሀ›› እስከ ‹‹ሰ›› ያለውን ስንመለከት የተሽከርካሪው ዓይነትና ሞዴል፣ የጭነቱ ልክ (በሰው፣በኩንታል፣በኪውቢክ ሜትር ወይም በሌትር ተለይቶ)፣ የቻንሲና የሞተር ቁጥሮች ፣ የሚጠቀመው የነዳጅ ዓይነት ፣ የተገዛበት ወይም የመ/ቤቱ ባለቤትነት ስር የዋለበት ቀን እና ዓ.ም፣ የተሽከርካሪው ዋጋ እና ፣ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር፤ እነዚህ የተጠቀሱት መረጃዎች በበቂ ምክንያት ተሟልተው ያልተገኙ እንደሆነ ባሉት መረጃዎች መሰረት ርክክብ ከተፈጸመ በኋላ ተጠቃሚው መ/ቤት ያልተገኙትን መረጃዎች ዝርዝርና ምክንያት በተሽከርካሪው የህይወት ታሪክ ውስጥ መዝግቦ ይይዛል፣ ያልተሟሉትን መረጃዎችም ተከታትሎ እንዲሟሉ መደረግ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ ኮሚሽኑ፡-

☞ የ41 ተሽከርካሪዎች የተገዙበት ወይም በኮሚሽኑ ባለቤትነት ስር የዋሉበት ቀንና ዓ.ም እንዲሁም ተሽከርካሪዎች የተገዙበት ዋጋ በማህደራቸው ባሉ ቅጾች ላይ

የሌለ ከመሆኑ በተጨማሪም ተሽከርካሪዎቹ በግዥ፣ በስጦታ እና በዝውውር ወደ ኮሚሽኑ ሲገቡ ሞዴል 19 የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠላቸው መሆኑ፤

☞ የመንግስት ተሽከርካሪዎችና ተጓዳኝ ዕቃዎች መረከቢያ (ቅጽ-01)፣ የመንግስት ተሽከርካሪዎች ዕለታዊ የነዳጅ፣ የዘይትና የኪ.ሜ መመዝገቢያ (ቅጽ-02)፣ የመንግስት ተሽከርካሪዎች ወርሃዊ የነዳጅ፣ ዘይት እና የጥገና ወጪ ማጠቃለያ (ቅጽ-03)፣ የመንግስት ተሽከርካሪዎች የህይወት ታሪክ መመዝገቢያ (ቅጽ-04)፣ የመንግስት ተሽከርካሪዎች ለተጠቃሚዎች መመደቢያ (ቅጽ-05)፣ የመንግስት ተሽከርካሪዎች አገልግሎት መጠየቂያና የመዘዋወሪያ ፍቃድ መስጫ (ቅጽ-06)፣ ልዩ መታወቂያ (ቅጽ-07)፣ የመንግስት ተሽከርካሪዎች የነዳጅ፣ የዘይትና ቅባት መጠየቂያ (ቅጽ-08)፣ የመንግስት ተሽከርካሪዎች የጥገና መጠየቂያ (ቅጽ-09) እና የተሽከርካሪዎች የአደጋ መግለጫ (ቅጽ-13) ቅጾቹ ተሞልተው በ41ዱም ተሽከርካሪዎች የግል ማህደር ውስጥ ያልተቀመጡ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

<u>የህግ ጉዳዮች በተመለከተ (Compliance Issue)</u>፣

1. <u>*በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ የታተመ ደረሰኝ ሳይቀርብ የተፈጸመ ግዥ*</u>

በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀፅ 19 እና 20 እንዲሁም በታክስ ደረሰኝ አጠቃቀምና አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 149/2011 አንቀጽ 9 በተገለጸው መሰረት ማንኛውም በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ የመጠቀም ግዴታ ያለበት ተቋም የሽያጭ መሳሪያው በጥገና ላይ ባለበት ጊዜ ካልሆነ በስተቀር በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ከታተመ ደረሰኝ ውጭ በሌላ ማናቸውም ዓይነት ደረሰኝ ሽያጭ ማከናወን እንደማይችል ይገልጻል፡፡ በዚህ መሰረት መ/ቤቱ ለሚፈፅመው ክፍያ ተገቢውን ደረሰኝ የሚቀበል መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ፡- በቀን 2/09/2014 ዓ.ም በወጪ ማስመስከርያ ቁጥር 9447 በሂሳብ መደብ 2211101 ከብስራት ተስፋዬ የጨርቃ ጨርቅ ልብሶች ችርቻሮ ንግድ የተለያዩ የደንብ ልብሶች ግዥ በብር 88,063.79 እና በቀን 2/09/2014 ዓ.ም በወጪ ማስመስከርያ ቁጥር 9447 በሂሳብ መደብ 2211101 ከገነት አዳሙ የአዋቂዎች አልባሳት የጫማና የቆዳ ውጤቶች ችርቻሮ ንግድ የሙሉ ልብስ በብር 103,500.00 ግዥ ሲፈጸም በማኑዋል ደረሰኝ ሲሆን አቅራቢዎቹ ማኑዋል ደረሰኝ እንዲጠቀሙ ከሚመለከተው ገቢ ሰብሳቢ

መ/ቤት ፍቃድ የተሰጠበት ደብዳቤ ሳይቀርብ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

2. <u>ለገቢዎች ሚኒስቴር ገቢ ያልሆነ የገቢ ግብርን በተመለከተ</u>

የፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ 979/2008 ዓ.ም ክፍል 10 አንቀጽ 97 ተቀንሶ የተያዘውን ግብር ስለመክፈል በሚለው አርዕስት ስር ን.አንቀጽ አንድ ማንኛውም ግብር ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ ያለበት ሰው ከሚከፍለው ገንዘብ ላይ ቀንሶ የሚያስቀረውን ግብር ክፍያ ከፈፀመበት ወር በኋላ ባሉት ፴ (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ መክፈል ይኖርበታል በማለት ይደነግጋል፡፡ ኮሚሽኑ በመመሪያው መሰረት ከተለያዩ ክፍያዎች ቀንሶ ያሰቀረውን የታክስ ገቢ በወቅቱ ለገቢዎች ሚኒስቴር ገቢ ማድረጉን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ፡- በድምሩ ብር 10,420.00 በተለያየ ጊዜ የጉልበት (የቀን) ሰራተኛ ቀጥሮ ሲያሰራ ቀንሶ ያስቀረውን ግብር ለገቢዎች ሚኒስቴር ገቢ ያላደረገ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

3. <u>መንግስትን ለተጨማሪ ወጪ የዳረገ ግዥን በተመለከተ፤</u>

የፌደራል መንግስት ግዥ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ 2002 በወጣው ክፍል አንድ አንቀጽ 4 ፊደል ሀ በግዥ አፈጻጸም ረገድ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም ማስገኘት እንደሚገባ ይህም ማለት ቁጠባን ፣የአፈጻጸም ብቃትን እና ውጤታማነትን ማረጋገጥ እንዳለበት መመሪያው ይገልፃል፡፡

ይሁን እንጂ ኮሚሽኑ ካሳንችስ የሚገኘው ቢሮው ውስጥ ለኖህ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማ የስቱድዮ ግንባታ ብር 1,867,194.00 እና ለኃይለሚካኤል አስፋው ህንፃ ሥራ ተቋራጭ የህንጻ እድሳት ብር 3,023,919.59 በድምሩ ብር 4,891,113.59 ወጪ በማድረግ ያሰራና ያስጠገነ ቢሆንም ምንም አይነት አገልግሎት ሳይሰጥ ሕንፃው ሙሉ በሙሉ እንደገና እንዲታደስ በመደረጉ የመንግሥት ገንዘብ ያለአግባብ ለብክነት የዳረገ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

4. <u>በውሉ ቀነ ገደብ እቃው ገቢ ባለመሆኑ ያልተቀነሰ የጉዳት ካሳ ቅጣት</u>

ሰኔ 2002 ዓ.ም በወጣው የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል 4 አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 27/3 (ሸ) መሠረት አቅራቢው በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ዕቃውን፣ የምክር አገልግሎቱን፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራውን ወይም አገልግሎቱን አጠናቆ ባያስረክብ፣ ላዘገየበት ጊዜ የሚወሰደውን እርምጃ በአቅራቢውና በመንግሥት

መ/ቤት መካከል በሚደረግ ውል መካተት እንዳለበት የተገለጸ ሲሆን በዚሁ መመሪያ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 27/4/ሀ መሰረት ደግሞ ክፍ ሲል በመመሪያው አንቀጽ 16.27.3 (ሸ) መሠረት አቅራቢዎች ግዴታቸውን ባይወጡ ግዴታቸውን ሳይወጡ ለዘገዩበት ጊዜ ሳይፈጽሙ በቀረው የውል መጠን ላይ በየቀኑ 1/1000ኛ መቀጣት እንዳለባቸው እና በዚህ ዓይነት የሚታሰበው መቀጫ የውሉን 10% መብለጥ እንዳሌለበት በግልፅ ተቀምጧል፡፡ በዚህ መሠረት ኦዲት ሲደረግ፡- ኮሚሽኑ በካሳንችስ ቢሮው ለሚያስገነባው ስቱዲዩ ግንባታ ከኖህ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማ ጋር ብር 1,867,194.00 ውል የገባ እና በቀን 25/02/2014 በወጪ ማስመስከሪያ ደረሰኝ ቁጥር 8005 በሂሳብ መደብ 2231103 ብር 1,039,804.61 ክፍያ የተፈጸመ ሲሆን በገባው ውል መሰረት ውል የተገባው 18/08/2013 ዓ.ም በ20 ቀን ውስጥ አጠናቆ በ7/09/2013 ዓ.ም ማስረከብ የነበረበት ቢሆንም ሳይት የተረከበበት 02/09/2013 ዓ.ም በመሆኑ ሳይቱን ከተረከበበት ጊዜ ጀምሮ በ20 ቀን ውስጥ አጠናቆ በ22/09/2013 ዓ.ም ማስረከብ ሲገባው ርክክብ የተፈጸመው በ02/02/2014 ዓ.ም በመሆኑ ላዘገየበት ለ134 ቀናት ብር 250,204.00 (1,867,194.00X134X1/1000) ቢሆንም የጉዳት ካሳ ከውሉ 10% መብለጥ ስለሌለበት መቀጣት ያለበት ብር 186,719.40 ሳይቆረጥ ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

5. <u>ግልጽ እና ተደራሽ ያልሆነ የግዥ ሂደትን በተመለከተ፤</u>

የፌደራል መንግስት ግዥ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ 2002 በወጣው ክፍል አንድ አንቀጽ 7/2 ፊደል ‹‹ሐ›› የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ የመወዳዳሪያ መስፍርቶቹ አድሏዊ ያልሆኑ፣ ግልጽ እና ተደራሽ መሆናቸውን የማረጋገጥ ሃላፊነት እንዳለበት መመሪያው ይገልፃል፡፡ ይሁን እንጂ ኮሚሽኑ በቀን 21/07/2014 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 9007 በሂሳብ መደብ 2251101 የሀገር አቀፍ የጸረ-ሙስና ፖሊስዎች፣ የሀገር አቀፍ የጸረ-ሙስና ስትራቴጂክ ሰነዶች እና የዳሰሳ ጥናት ለማስተርጎም ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህራንን ሲያወዳድር ለዩኒቨርሲቲው በቀጥታ መስፈርቱን የሚያሟሉ መምህራን እንዲልክለት ዩኒቨርሲቲው በመጠየቅ ከሚያገኘው መረጃ መሰረት በውድድሩ መሳተፍ የሚፈልጉትንና የኮሚሽኑን መስፈርት የሚያሟሉ መምህራኖች በመጋበዝ አወዳድሮ አሸናፊውን መምረጥ ሲኖርበት ኮሚቴው ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋ ባለሞያዎች ዘንድ በመሄድ 4 መምህራኖችን ዋጋ እንዲያቀርቡ በማድረግ ዶ/ር ደጀኔ ገብሬ ባቀረቡት ዝቅተኛ

ዋጋ መሰረት አሸናፊ የተመረጠ ሲሆን መምህራኖቹ በምን መስፈርት እንደተመረጡ የሚገልጽ ማስረጃ በሌለበት እና ግልጽና ተደራሽ ባልሆነ መስፈርት አወዳድሮ ግዥ በማከናወን በድምሩ በብር 71,000.00 ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ በኦዲት ወቅት ታውቋል፡፡

6. <u>የገበያ ጥናት ሳይኖር በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ የተገዛ ግዥ፤</u>

ሰኔ 2002 ዓ.ም በወጣው የፌደራል መንግስት የግዥ አፈጻፀም መመሪያ ክፍል ሁለት አንቀፅ 8 ንኡስ አንቀፅ 24(8) መ/ቤቱ በዋጋ ማቅረቢያ በተደጋጋሚ ለሚፈፅማቸው ግዥዎች በኤጀንሲው ድህረ ገፅ የሚያወጣውን ወቅታዊ የዋጋ ዝርዝር፤ በግዥ ስራ ክፍሉ የሚካሄድ የገበያ ጥናት በመጠቀም ዝቅተኛ ተብሎ የሚመረጠው ዋጋ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ መሆኑን ማመን እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ ኮሚሽኑ በተለያዩ ቀናት በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ ግዥ ሲፈፀም በግዥ ስራ ክፍሉ የገበያ ጥናት ባለሙያ የሌለውና በኤጀንሲው ድረ-ገጽ ከሚወጣው ወቅታዊ ዝርዝር ዋጋ ጋር ሳይመሳከር ዝቅተኛ ተብሎ የሚመረጠው ዋጋ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ መሆኑን ሳይረጋገጥ በድምሩ ብር 789,931.87 በዋጋ ማቅረቢያ ግዥ በማከናውን ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

7. <u>ለሶስተኛ ወገን የተሰጠ የጥበቃ እና የጽዳት አገልግሎትን በተመለከተ፤</u>

የፌዴራል የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁ.1064/2010 አንቀጽ 22/1 አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ማንኛውም መ/ቤት ሚኒስቴሩን በማስፈቀድ የህዝብን ጥቅም በማይጎዱ የተወሰኑ የስራ መደቦችን ወይም ሥራዎችን ለግል ድርጅቶች ወይም ለሌሎች ተቋማት በውል በማሸጋገር እንዲሰሩ ማድረግ እንደሚቻል ይደነግጋል፡፡ እንዲሁም የፌዴራል መንግስት ግዥ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ 2002 በወጣው ክፍል አንድ አንቀጽ 4 ፊደል ሀ በግዥ አፈጻጸም ረገድ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም ማስገኘት እንደሚገባ ይህም ማለት ቁጠባን፣ የአፈጻጸም ብቃትን እና ውጤታማነትን ማረጋገጥ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ ኮሚሽኑ ከህዳሴ ቴሌኮም አ.ማህበር የጽዳት አገልግሎት እና ከታአግ የጥበቃና የሰው ኃይል አገልግሎት ኃ.የተ.የግ.ማ የጥበቃ አገልግሎት ሲፈጽም፡-

- ወደ ግዥ ሂደቱ ከመግባቱ በፊት ስራዎቹን ለሶስተኛ ወገን ለማሸጋገር ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ፈቃድ ሳይጠየቅ ስራዎቹ ለሶስተኛ ወገን የተሰጡ መሆኑ፣

- ስራዎቹ ለሶስተኛ ወገን ከመሰጠቱ በፊት ከሰው ሃይል እንዲሁም ከመንግስት ውስን ሃብት አኳያ የአዋጭነት ጥናት የተሰራበት ማስረጃ የሌለ መሆኑ ፣
- ቋሚ ከሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በተፈቀደ መደብ ላይ የተቀጠሩ 12 የጽዳት ሰራተኞች እና 1 የጽዳት ሰራተኞችን ተቆጣጣሪ እንዲሁም 15 የጥበቃ ሰራተኛ እና 1 የጥበቃ ሰራተኞችን ተቆጣጣሪ በተፈቀደ መደብ ላይ እያሉ ተጨማሪ ሁለቱንም ስራ ለሶስተኛ ወገን አስተላልፎ መሰጠቱ መንግስትን ለተጨማሪ ወጪ የዳረገ መሆኑ፤
- ለኮሚሽኑ ጽዳትና የጥበቃ አገልግሎት ስራ ሃላፊነት ሲሰጥ ኮሚሽኑ ምን ምን ስራዎችን ማረጋገጥ እንዳለባቸው ማለትም ከሰው ሃይል እና ከግብዓቶች ቁጥጥር አንጻር ወጥ የሆነ የአሰራር መመሪያ የሌለ መሆኑ፣

በድምሩ ብር 1,071,850.00 የግዥ ሂደቱን ሳይከተል የጽዳትና የጥበቃ አገልግሎት ግዥ ከሶስተኛ ወገን በማከናወን ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

8. <u>ከበጀት በላይ የወጣ ሂሣብ በተመለከተ፤</u>

የፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 ክፍል ሶስት አንቀጽ 12(1) ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ለበጀት ዓመቱ የተፈቀደለትን የመደበኛም ሆነ የካፒታል በጀት አጠቃቀም በሚገባ መቆጣጠር እንዳለበት ይገልጻል።በተጨማሪም በፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6/2 መሠረት የበጀት ዝውውር ወይም ተጨማሪ በጀት ካልተፈቀደ በስተቀር ለአንድ የመንግስት መ/ቤት በሂሳብ መደብ ተለይቶ ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ መፈፀም እንደማይቻል ይገልጻል፡፡ በዚሁ መሰረት የኮሚሽኑ በጀቱን የሚቆጣጠር መሆኑን ለማረጋገጥ የ2014 በጀት ዓመት ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተፈቀደው ከ10% በላይ ሥራ ላይ ከዋለው ጋር ሲነጻጸር፡- በድምሩ ብር 961,512.66 የመደበኛ በጀት የበጀት ዝውውር ሳይደረግና ሳይፈቀድ ከተፈቀደ በጀት በላይ ወጪ የተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት